# ዝምታው ይቁም

## ስያሚያችን ኢወክንድ

## ልሳናችን ነቅንቅ

የዓለም ወጣቶችን እንቅስቃሴ ገድል ስንፈትሽ የኢትዮጵያ ተማሪዎች የትግል ታሪክ ደኅስ ያለውን አኩሪ ምዕራፍ ይይዛል ። እነሆ የፊታችን ሳምንት አስገምጋሚው የየካቲት ስልሳ ስድሰት ዝክረ ትግል ይጠብቀናል ። የካቲት ስልሳ ስድስት ይደገም የሚል መግለጫ ባለፈው አወጥተን ነበር ዛሬ ደግሞ በቁርጠኝነት ይደገማል የሚለውን መፈክር ስናስተጋባ ከኢትዮጵያ ሰፊው ሕዝብ አበራክ ተወልደን በአይገበሬው ኢሕአፓ ተኮትክተን ለዚህ የበቃን የ ኢትዮጵያ ወጣት ደጀንነታችንን በኩራት እየገለፅን ነው ።

መቼም ይሁን መች ድቀት ለአምባገነኖች የማያልፏት እጣቸው ነችና ዛሬ ከሰሜን አፍሪካዊቷ ቱኒዚያ የ 26 ዓመት ወጣት የለኮሰው የነፃነት ሻማ ተቀጣጥሎ የባለሰለሣ ዓመታት ሥልጣን ስዶችን እያሳደደና እየቃጠለ እንደሚገኝ ሁሉም ተከታትሎታል ። ታድያ ከትናትና ወዲያ ቱኒዚያ ትላትና ግብፅን ዛሬ የሱዳን ወጣቶችን ያነሳሳ ሕዝባዊ አመፅ ነገ በ ኢትዮጵያችን እንደሚደገም የሚጠራጠሩ ካሉ ቤተመንግስት የተወተፉ ዘመናዊ ወያኔዎችና ነፃነታችውን በፍርፋሬ የሸጡ ተለጣፊዎች ብቻ ናቸው ።

የኢትዮጳያ ወጣቶች ሆይ !!

ይህንን ጥሪ ስናሰማ ለሐተታ ግዜ ስለሌለን ነው በአጭር ያደረግነው ። ከላይ ከተጠቀሱት ሕዝባዊ አመፅ ከተፋፋመባችው የአፍሪካ አገሮች በባሰ መልኩ በገዛ ሀገሩ ባዳ የሆነ ዜጋ ከኢትዮጳያ ሕዝብ በላይ የለም ።

እየጋፍነው ያለው የማያሽር የግፍ እንቆቆ ነውና እማኝ አንቆጥርም ። የትውልድም የሀገርም አደራ ያረፈብን የጀግናው የኢትዮጳያ ልጆች ነንና ታሪክ መሥሪያችን ጊዜ ከፊታችን ድቅን ብሏል ።

በነፃነታችን ለይ ላለፉት 20 ዓመታት ያናጠረብንን ዘረኛ ፤አማቂ ፤ ሙሰኛ፤ ክብር አዋራጅ ፤ ህፃንንና መሬት ሻጭ ሥርዓት በሕዝባዊ አመፅ ለመናድ ዝግጁ እንሁን ። በተከታታይ ዘመናዊ ቴክኖሌጂ በፈጠራቸው መገናኘዎች በመከታተል ለምንጠራው ቁርጥ ያለ ዝምታ ሰባሪ አዎጅ በተጠንቀቅ ዘብ እንቁም ። የኢትዮጳያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ወጣቶች ክንፍ ድርጅት አባላት በያላችሁበት ክፍለ ሀገራት ይህ የተጠንቀቅ የሕዝባዊ አመፅ ጥሪ እንደደረሳችሁ ለዜጋ ሁሉ እንድታስተላልፉ አደራ እንላለን ። በተለይ በሳምንት ሁለት ቀን ረቡዕና እሁድ በሚተላለፈው የናት ድርጅታችን የኢሕአፓ ድምፅ በሆነው በፍኖተ ዲሞክራሲ የኢትዮጳያ አንድነት ድምፅ እንድትከታተሉት በሕዝባዊ ፍቅር መልዕክታችንን እናስተላልፋለን ።

ሕዝባዊ አመፃችን በቅርብ ይጠራል !!!

ታሪካዊ የየካቲት ስልሳ ስድስት ይደገማል !!!

የ ኢትዮጳያ ወጣቶች ለስርዓት ለውጥ ተዘጋጅተናል !!!

ኢወክንድ

ጥር 2003 ዓ.ም.ድ

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: joineprpyl@google.com
www.eprpy.com